# በቁስላችን ላይ ጨው መነስነሳችሁን አቁሙ እንበል

(ከመርካቶ ላፍቶ)

ላለፉት 20 ዓመታት በላይ በ'ምን ትሆናላችሁ!' ኢትዮጵያን ጨምዶ የያዘው የወያኔ አገዛዝ፣ እየቀለደብን መሆኑን እንደገና መንገር የሚያስፈልግ አይመስለኝም። እንደገባ በአዲስ አበባ አደባባይ ወጥተው የተቃወሙ ወጣቶችን፣ የኤርትራን መገንጠል ደግፎ (እንዲሳካ) ሽር ጉድ ይል የነበረውን ቡጥሮስ-ቡጥሮስ ጋሊን የተቃወሙ ዜጎችን አላግባብ በመቀጥቀጥ ባቆሰለና በገደለ ጊዜ የሰጠው ምክንያት፣ "የሰልፍ መበተኛ ትጥቅ የለንም፣ ሰዎቻችንም ዝግጅቱ የላቸውም" የሚል ነበር። እንደገና ከ15 ዓመት በኋላ በ1997 ግንቦቱ ምርጫ ወጣቶችን ባደባባይ፣ በጠራራ ጸሐይ ሲረሽን ያንኑ ምክንያት እንደገና አቀረበ። ይህም ብቻ አይደለም ጭራሽ መንግሥትን በአመጽ ሊገለብጡ የሞከሩና ለዚህም ተባባሪ የነበሩ፣ አለያም በዚያ ተቀስቅሰው አደባባይ የወጡ ነበሩና ለደረሰው ያካል ጉዳትና ሞት ተጠያቂው እኔ አይደለሁም ብሎ ደነፋ። መደንፋት፣ መደብደብ፣ ማሰር ሳያንሰው ባስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመንቀሳቀስ መብትን ገድቦ፣ ጥፋተኞቹ፣ የሁከቱ ቀስቃሾች የተቃዋሚ መሪዎቹ ናቸው በማለት (የተቃዋሚ መሪዎችን) ለቃቅሞ እስር ቤት አጎራቸው። በረከትማ በመጽሐፉ የከተማ በተለይም የአዲስ አበባ ነዋሪ ለነበረው ትርምስ ተባባሪ ነው ይለናል። ከዚያ በኋላ እሱው ቀማኛ እሱው ዳኛ በሆነ ሥርዓቱ አማካይነት፣ ከግንቦት 1997 ምርጫ በኋላ የሆነውን የምናውቀው ነው።

በስንት አጥንትና ደም፣ እንዲሁም በስንት ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ተከብሮ የቆየውን የሀራችንን ዳር ድንበር ሲንድና ጠቀም ያለ የመሬት መጠን ለሱዳን አሳልፎ ሲሰጥ፣ አሁንም ምንም ያረኩት ነገር የለም "ዘለቄታዊ ሰላም" ከሱዳን ጋር እንዲፈጠር አረኩ እንጂ ብሎ - አዎን አርጌዋለሁ ምን ትሆናላችሁ ዓይነት። በዚህ ጊዜም መጠነኛ ተቃውሞ ቢታይም፣ ለም መሬታችን ለሱዳን ሲሰጥ፣ በዚያ ላይ የኖረው ዜጋችን የትም ሲጣል ምንም እንዳልሆነ ነገር ታለፈ። አሁንም ምን ትሆናላችሁ የሚለው ንቀቱ እንደሠራለት ተማምኖ፣ ወደሌላ የጥፋት ምዕራፍ ዘለለ። መሬትን ለውጭ ሃብታሞች ይህ ነው በማይባል የወደቀ ዋጋ በሄክታር፣ እጅግ በጣም ረጅም ለሆነ የሊዝ ዓመት መቸብቸብ ውስጥ ገባ። ይኸን እንዳላየ እንለፈው ብንል እንኳን ዜጎች ከኖሩበት ለም መሬታቸው እየተፈናቀሉ ለይስሙላ

"የለውጥ" (<u>ያልተመጣጠነ</u> ልዋጭ) መሬት ሰጠኋቸው እያለ በቂ መቋቋሚያ ሳይደረግላቸው የትም ሲጣሉ ስናይ ዝም ማለት ይቻላል? እነዚህ የውጭ ሃብታሞች በተረከቧቸውና ባቋቋሟቸው እርሻዎች ላይ የሚሠሩ ሠራተኞች ተገቢ የሠራተኛ መብታቸውን ባላከበረ ሁኔታ እጅግ በጣም በዝቅተኛ ክፍያ እንዲሠሩ ሁኔታው ተመቻቸ። ያለማጋነን ላዲስ ባርነት ተዳረጉ - ይህንንስ ዓይን እያየ አላየሁም ጆሮ እየሰማ አልሰማሁም ማለት ይቻላል?

ሰዎችን ወደሌላ ማስፈርን ከነካካን አይቀር ወያኔ የሥልጣኑን ኮርቻ ከመያዙ በፊት በኮሎኔሉ መንግሥት የተካሄደውን የሠፈራ ፕሮግራም፣ በህዝቡ ላይ ካለፈቃዱ የሚካሄድ እርምጃ ነው በሚል ትልቅ መቀስቀሻው አርጎት እንደነበር እናስታውሳለን። አልፎም በተለይ ትግራውያን ላይ ያነጣጠረ ነው በሚልም በየውጭ ሚዲያውና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዘንድ ለራሱ የፖለቲካ ፍጆታ (በማጭበርበሪያነት) ምን ያህል እንደተጠቀመበት የቅርብ ጊዜ (የማጭበርበር) ትዝታ ነው። ዛሬ ወያኔ 70 ሺህ ሠፋሪዎች በተሟላ የጤና አገልግሎት፤ ትምህርት ቤት ደግሞ ለልጆቻቸው ተዘጋጅቶላቸው ተምበሽብሸዋል እያለ በሚዲያው ቢያደነቁረንም ዕውነቱ ምን እንደሆነ ግን በተለይም በጋምቤላ አካባቢ ያለው ህዝባችን እያለቀሰ ብሶቱን እያሰማ ነው። የተዘጋጀም ነገር የለም፤ የትም ወድቀን ብርድና ሃሩሩ ይጫወትብናል፤ ኑሯችን እንዳለ ተመሰቃቅሎብናል። ወዴት ሄደን ለማን አቤት እንደምንልም ግራ ገብቶናል እያለ ነው እንዲሰፍር የተደረገው ዜጋችን። ባንጻሩ ከለም መሬቱ ሲነቀል ማንም ሃሳቡን አልጠየቀውም፣ አላማከረውም - እናሠፍርሃለን፤ የምንልህን ተቀብለህም ትሠፍራለህ ከመባሉ በቀር!

ከዚህ መሬትን ለውጭ ሃብታሞች በነመለስ መቸብቸብ ጋር በተያያዘ፣ ሌላው የዓለምን የልማትና የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችን ሳይቀር እያስገረመና እያነጋገር ያለው በሊዝ ከተሰጠው መሬት የሚገኘውን ምርት አንድ ሳያስቀሩ ማውጣት እንደሚችሉ መቀመጡ ነው። የመገረሙ ነገር ለእነዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሆነ ለእኛም አለምክንያት አይደለም። በተደጋጋሚ ህዝባችን ለአስከፊ ረሃብ እየተጋለጠና በረሃብ እየረገፈ፣ ሀገራችን በረሃብ የመርገፍ ምሳሌ ሁና እየተጠቀሰች፤ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ "ተርበናልና ድረሱልን!" ጥሪ እንደሃገር ስናሰማ የቆየን መሆናችን

የታወቀ ነው - በነመለስ ጭምር ያውም ከ20 ዓመት በፊት ብቻ ሳይሆን ትናንት በ2003 ዓመተ ምህረትም የድረሱልን ጥሪውን አይተናል!

ሌላም አለ፤ ወያኔ የሥልጣን ወንበሩን በተፈናጠጠ ሰሞን (መለስ) ስለባንዲራችን ጨርቅነትነገረን። ቆየት ብሎ ደግሞ የአክሱም ሐውልት ለጋምቤላው ወይም ለወላይታው ምኑ ነው በማለት መሳለቁንና ብሔራዊ እሴቶቻችንን እንዲህ አርጎ በማጣጣል፣ በምን ትሆናላችሁ እንደደነፋ እናስታውሳለን። አቦይ ስብሃት የሚባሉት ደግሞ፤ ወያኔ ስለኤርትራ መገንጠል (እነሱ ነፃ መውጣት ነው የሚሉት) የነብረውን ሚና ተጠይቀው ሲመልሱ፤ ህወሓት ስለኤርትራ ትክክለኛ አቋም እንደነበረውና ለዚያም እንደታገለና ተገቢውን የህይወት አስተዋጽኦ እንዳደረግም በኩራት/በድፍረት መናገራቸው ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ኤርትራን እነካለሁ ለሚል የምንታገለው እኛ ነን፤ ዕወቁት፤ ድንፋታውን ባደባባይ ተናግሯል።

እነዚህን ከላይ ከተጠቃቀሙትና ሌላም ልብን ከሚያቆስል ግብራቸው ሳናገግም፤ በቅርቡ ደግሞ እኝሁ አቦይ ስብሃት ተብዬ "በቁስል ላይ ጨው መነስነስ ዓይነት" አዲስ የኢትዮጵያን ታሪክ ክህደት ቀባጥረዋል። ይኸውም ሌላ ብሥራት አማረ የሚባል ወያኔ የአክሱምን ኢትዮጵያዊነት ጥያቄ አብጠልጥሎ መጻፉን አስመልክቶ ስለዚሁ በቪኦኤ ትግርኛው ፕሮግራም ለቀረበላቸው ጥያቄ፤ አክሱም ከኤርትራና ትግራይ ውጭ ላለው ኢትዮጵያዊ ምኑም አይደለም። ከዚያም በላይ ዕውነት አክሱም ስንል አሁን ስላለው ትግራይ የሚናገር አይመስለኝም በሚል በማጣጣል፤ አልፎም ተምቤንና አጋሜ የአክሱም አውራጃ ነበሩ እንዴ? ታሪክ አንበውም አጋሜ የአክሱም አካል እንዳልነበረ ግንዛቤ ላይ እንደደረሱ ጭምር ተመጻደቁ፣ በቃለ መጠይቃቸው።
ታዲያ ጥያቄው እኮ እራሳቸው አቦይ ስብሃት የህወሓት ሊቀመንበር በነብሩበት ወቅት ጭምር የ'ህወሓት' (TPLF) አርማው የአክሱም ሓውልት ነበር። ታዲያ ያኔ ሐውልቱ (የሚታገሉትስ) ለየትኛው ትግራይ ነበር? በዚህ ሁሉ ውስጥ ህወሓት ለኢትዮጵያ የሚለውንማ እንግዲህ ጨርሰን ከጭንቅላታችን እናውጣው ማለት ነው!

የነኝህ አገር አጥፊ ጉዶች አስከፊና ታሪክ አጉዳፊ፣ ህዝብን የሚያዋርድ ሥራ ተነግሮ፣ አያልቅምና ይህን የመሰለ ሥራቸው እንዳይቀጥል አንድ ነገር ማረግ አለብን። በዚህ ላይ ብዙ ተብሏል፤ አሁንም መፍትሄው አንድና አንድ ብቻ ነው። ጠንክረን ልንታገላቸውና ልናስወግዳቸው መነሳት፣ መታገል! ለሀገር ለወገን የምንል ሁላችን እንነሳ፣ በተጨባጭ እንተባበር፣ እንታገል፤ "በቁስላችን ላይ ጨው መነስነሳችሁን አቁሙ!" ብለን እናሽቀንጥራቸው።